

# የዶክተር ቤይሊ የመንግሥተ ሰማይና የዘላለም ፍርድ ልምምድ

http://www.zionfellowship.org

በረዥሙ ህይወቴ ጌታ እጅግ በጸጋው ብዛት ብዙ ራእዮችን ሰጥቶኛል። አንዳንዶቹን በጣም በቅርቡ በጻፍኳቸው "የገነት ክብር እና ያልተነገሩት የሲዖል ሽብሮች" በተባሉት መጻሕፍት ላይ አካፍያቸዋለሁ። አሁን ሁለቱን በድጋሚ ልመለስባቸው እወዳለሁ።

ጌታ ይህ የመጀመሪያው ልምምዴ ሕዝቦቹን ስለመጨረሻው ፍርድ እንዳስጠነቅቃቸው ግልጽ አድርጎልኛል።

## እግዚአብሔር ለህይወትህ(ሽ) ያለውን እቅድ ፈጽመሀል(ሻል)?

በሠላሳዎቹ አጋማሽ እድሜዬ ላይ ሳለሁ፥ ምንም እንኳን የጴንጤቆስጤ አገልጋይ ብሆንም፥ የሜን ላይን ወንጌላውያን ቤተክርስቲያን መጋቢ እንድሆን ተጋበዝሁ። ጌታ ባርኮን፥ ጉባኤው ሰፋ እኔም በከተማዋ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን እንዳከናውን ግብዣ ተደረገልኝ። ከዚያም ጌታ ቤተክርስቲያኒቱን አስመልክቶ የመጀመሪያ ምልክቱ በልሳን መናገር ሆኖ ስለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንድናገር ከነገረኝ በኋላ ሁሉም ነገር ተቀየረ። ለጌታ ቤተክርስቲያኒቱ ልትከፋፈል እንደምትችል ነገርሁት። እርሱም "*አውቃቸዋለሁ፥ ነገር ግን አንተን ላውቅህ እፈልጋለሁ። የእኔን መልእክት ትሰብካለህ ወይስ እነርሱ መስማት የሚፈልጉትን መልእክት?*" ጉባኤው መስማት የሚፈልገው ቀለል ያሉ የወንጌል ታሪኮች ያሉባቸውን መልእክቶች ነው።

ከዚያም የእርሱን መልእክት ለመስበክና መልእክተኛው ለመሆን ለጌታ ውሳኔን ወሰንሁ። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት መስበክና ማስተማር ጀመርሁ። ምንም እንኳን ብዙዎች ትምህርቱን ቢቀበሉትም፥ ቤተክርስቲያኒቱ ግን ተከፈለች። በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች ብቻ አይደሉም፥ ነገር ግን ቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ እንኳን የማይካፈሉት የከተማዋ ሰዎች ጭምር ተቃወሙኝ። ሰዎች ከእኔ ለመሸሽ በመንገድ ወደ ሌላኛው አቅጣጫ መሻገር እስኪጀምሩ ድረስ ደረሰ።

የዚህ ሳይቀበሉት-የመቅረት( rejection) ተጽዕኖ በአዕምሮዬና በልቤ እስኪሰማኝ ድረስ ትልቅ ጫና ፈጠረብኝ። ይህ ጫና ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ መተንፈስ ይቸግረኝ እንዲሁም በአገልግሎት ሥራዬ ላይ ትኩረት ማድረግም ይከብደኝ ነበር። በጭንቀቴ ውስጥ "*እባክህ ውሰደኝ!*" ብዬ ወደ ጌታ ጮኽኩ።

ከሁለት ወይም ሦስት ቀናት በኋላ፥ ሌሊት 9:00 አካባቢ ነቃሁ። ከአልጋዬ በላይ አንድ መልአክ ቆሞ ነበር። ከሰውነቴ ወጣሁና ከመልአኩ አጠገብ ቆምሁ። ወደ ባለቤቴ ተመለከትሁ፥ በትክክል ትተነፍስ ነበር፥ ነገር ግን እኔ ህይወት አልባ ነበርሁ። ከዚያም የህይወቴ ማብቃት እውነታ ጨምድዶ ያዘኝ። በምድር ላይ ለኢየሱስ ምንም ተጨማሪ ነገር ማድረግ አይቻለኝም። የሚያስለቅስና የሚያሳዝን ነበር። በስሜት የተሞላ ልምምድ ነበር።

ከዚያም ምንም ቃል ሳይናገር፥ መልአኩ ዞረ፥ እኔም ዞርሁ። ከዚያም ሙሉ በሙሉ በመልአኩ ቁጥጥር ውስጥ እንደሆንሁ አወቅሁ። ወደ ላይ ተመለከተ፤ እኔም ወደ ላይ ተመለከትሁ። ከዚያም በቤቱ ጣሪያ ውስጥ አልፈን ወደ ላይ መሄድ ጀመርን፥ (*ጣሪያው*) በፊታችን የሚሟሟ ነበር የሚመስለው። ከብርሃን በፈጠነ ቅጽበት፥ ጨረቃን ቀጥሎም ከዋክብትን አለፍናቸው፤ ወደ ገነት በፍጥነት እየሄድን ነበር። በመጀመሪያ የገነት መግቢያ ራስን በሚያስት መልኩ ወደ እይታ መጣ ከዚያ እየጠራ እየጠራ መጣ። እንደዛም ሆኖ እየቀረብን እየቀረብን ስንመጣ፥ ኀዘን ልቤን ጨምድዶ ያዘኝ። እነዚያን የገነት ደጆች ማየት ለእኔ ምንም ደስታ አልነበረም። (ለምን እንደሆነ ወደ በኋላ ላይ አስረዳለሁ።) ከዚያም በበሮቹ ፊት ለፊት ደረስን ነገር ግን *(ወደ ውስጥ)* አልገባንም። ይልቁንም መልአኩ በአጠገቤ እንዳለ፥ ህይወቴ በዓይኔ ፊት ሲያልፍ አየሁት። ይህም በግራዬ በኩል

ተከታታይነት እንዳለው ምስል ሆኖ አለፈ። ከውልደቴ ሰዓት ጀምሮ እስከ ሞቴ ሰዓት ድረስ፥ ነገር ግን፥ አንዳንዶቹ ምስሎች ባዶ ነበሩ። እነዚህ እንደተረዳሁት በህይወቴ እግዚአብሔርን ይቅርታ የጠየቅሁባቸው ቅጽበቶች ነበሩ፥ እናም ስለዚህ አሁን ምንም የተመዘገበባቸው ነገር የለም።

ህይወቴን እንዳየው ተደረገ። እነዚህንም ሁሉ ተረዳሁ። ወደ ገነት እየሄድሁ የነበረው **በደሙ** ስለተዋጀሁ፥ ዳግም ስለተወለድሁ፥ በውኃና በ*መንፈስ ቅዱስ* ስለተጠመቅሁ ነበር። በተጨማሪም የጽድቅ ሰባኪ ነበርሁ እናም በእርሱ ጸጋ፥ እሰብክ የነበረውን ህይወት ኖሬአለሁ፤ እንደዛም ሆኖ ግን ልቤ አሁንም በኀዘን ተሞልታለች።

ከዚያም በዚያን ጊዜ ግልጽ ሆኖልኝ ያልነበረ አንድ እውነት መረዳቱ ተሰጠኝ። በዓይኖቼ ፊት፥ ከምድር መሰረቶች መጀመሪያ እግዚአብሔር በህይወቴ የነበረው እቅድ ነበር፥ እናም ያለ ጊዜዬ ነበር እየሞትሁ የነበረው። ስለዚህ ለህይወቴ የነበረውን እቅድ አላሳካሁም። ኀዘኑ ልቋቋመው የማልችለው ከመሆኑ የተነሣ በመንፈሴ "*እባክህ ጌታ ሆይ፥ መልሰኝና ሌላ እድል ስጠኝ*" ብዬ ጮኽኩ። በእርግጥም ጩኸቴ ተሰምቶ ነበር። ምንም እንኳን እኔ ድምጹን ባልሰማውም፥ መልአኬ ነበር የሰማው።

ዞረ፤ እኔም ዞርሁ፥ አሁንም ድረስ በእርሱ ቁጥጥር ስር እንደሆንሁ። በጋራ ወደ ታች ሄድን፥ በግልጽ እንደሚታየኝ ቁልቁል ወደ ምድር። በድኃሚ እንደ ሚሚሚ በመሰለው በጣሪያው በኩል አልፈን ወደ ማረፊያ ክፍል ደረሰን። ከአልጋዬ በላይ ቆምን። ባለቤቴ አሁንም በሰላም ተኝታለች ከጎኗ ደግሞ፥ የሞተው ሰውነቴ። መልአኩ ሰውነቴን ነካው፥ እኔንም ነካኝ፥ ከዚያም ተመልሼ ወደ ሰውነቴ ገባሁ።

በኋላ ላይ ጌታን ለምን ይህ ልምምድ እንዳስፈለገ ስጠይቀው፥ ምላሹ "***ሕዝቤን ስለዘላለማዊ ፍርድ እንድታስጠነቅቃቸው ነው። በሥጋ የተሠሩትን ነገሮች ብቻ አይደለም (በእነዚያ ምስሎች ውስጥ የታዩት)፥ በተጨማሪ ደግሞ ከምድር መሠረቶች በፊት በእግዚአብሔር ለህይወታቸው የታቀደውን እቅድ የፈጸሙብት መጠንም ጭምር ነው።***"

እቅዱ የሚገለጥልን እስካሁን በተገለጠልን በመታዘዝ በሄድንበት መጠን ነው። በዚያ በፍርድ ቀን፥ ለህይወታቸው ካለው እቅድ በአጭር እንደቀሩ ብዙዎች በኀዘን ይረዱታል።

## ድቅድቅ ጨለማ

ብዙውን ጊዜ "*ሲዖል የት ነው?*" እየተባለ ይጠየቃል። መጽሐፍ ቅዱስ መልሱን ይሰጠናል፡ "በምድር የታችኛው ክፍል ውስጥ ነው።" በሌላ አባባል፥ ከስራችን ከምድር ገጽ በታች ነው። የቅርብ ጊዜ ልምምዴ ይህንን ያስረዳል።

"የክርስቶስ ህይወት" የሚል መጽሐፍ እየጻፍሁ ነው። የክርስቶስ አገላለጽ እጅግ የከበረ እንደሆነ የተሰማኝ ቦታ ላይ ደረስሁ። እንግሊዛዊ እንደመሆኔና፥ ካለኝ መጠነኛ የነገሥታት ቤተሰብ ቋንቋ እውቀት፥ (እ.ኤ.አ) በ14ኛው ክፍለ ዘመን የኖረ ንጉሥ እየመረዋሁ ነበር። እርሱን አስመልክቶ ለመጻፍ፥ በአፓርትመንቴ (በቤቴ) ውስጥ ምድር ቤት ውስጥ ሳለሁ ነበር፥ መሬቱ ተከፍቶ ራሴን በድቅድቅ ጨለማ መሀል ያገኘሁት። (ሐዋርያው ይሁዳ የገለጸው ይህን የሲዖል ክፍል ነበር።)

በዚህ ጊዜ በራዕይ ስላየኋቸው የተለያዩ የሲዖል ክፍሎች ማብራራት እፈልጋለሁ፤ የእሳት ባሕርና መድረሻ የሌለው ጥልቅ (ጥልቁ) ጥቂቶቹን ለመጥራት ያህል ናቸው። ነገር ግን ይህ ራእይ አልነበረም። በሲኦል **ውስጥ** ነበርሁ። ጨለማው ድቅድቅ ከመሆኑ የተነሣ የሚሰማ ነበር። የማይጣስ ነው።

በዚህ ምድር ላይ፥ ከሌሊቱ ጨለማ በሚባለው ጊዜ እንኳን፥ ዓይኖች ራሳቸውን ከጨለማው ጋር ከአስተካከሉ በኋላና አንድ ሰው በጨለማው ውስጥ ሊሄድና ነገሮችን ሊለይ ይችላል። ሆኖም ግን በዚህ የሲኦል ክፍል ይህ

የማይቻል ነው። በእርግጥም እጅግ የጠቆረ ጨለማ ነው። አንድን ሰው ጭምድድ አድርጎ የሚይዝ የፍርሀት ስሜት ያለበት ጨለማ ነው።

እኛ ሁላችንም፥ ቢያንስ በህይወታችን አንድ ጊዜ፥ ሕፃን እያለን ወይም ካደግን በኋላ፥ ሌሊት ብቻ ሊያመጣው የሚችለውን ፍርሀት ተለማምደናል (አጋጥሞናል)። ጨለማዎቹ የማይጣሱት የአፍሪካ ጫካዎች፥ የሌሊቱ (በጫካው ያሉት) ፍጥረታት (እንሰሳት፣ ወዘተ) ሲመጡ እጅግ የሚያስፈራ ቢሆንም ሁል ጊዜ ግን ጨለማው የማለዳዋ ፀሐይ ስትወጣ ስፍራውን እንደሚለቅ ተስፋ አለ። በተወሰኑ ሰዓታት የብርሃንን ጨረሮች ትጠባበቃላችሁ። ምንም ብርሃን በሌለበትና ከአሁን አሁን የሆነ ነገር ይሆናል የሚል ፍርሀት ባለበት በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ምንም ተስፋ የለም።

በዚያ ለምን ያህል ጊዜ ነበርሁ አላውቅም። ሰዓት ያለ አይመስልም። በጨለማው ጽናት ውስጥ ስሄድ፥ የሆነ አካል ወደ እኔ መጣ። አክሊል በራሱ ላይ ደፍቶ እንደ ንጉሥ የለበሰ ነበር። ምንም እንኳን ካለፉት መቶ አመታት በፊት ከነበሩት ቢሆንም ፥ ማን እንደነበረ አወቅሁ። በገነትም ይሁን በሲኦል፥ ስሜቶቻችን የእውነት ሁኔታዎችንና ሰዎችን የመለየት ስሜታችን በጣም ትክክል ይሆናል።

እንደተማረና እንደ ጨዋ ሰው አመለከተኝ። “መልካም ክቡር ሆይ፦” አለ፥ “ወደ ብርሃን የሚወስደውን መንገድ ልታሳየኝ ትችላለህ?” ልመልስለት የምችለው ብቸኛው መልስ መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ ነበር: “ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፦” (ዕብራውያን 9፥27)። በዛ በቀላሉ እርሱን ይዞት የመጠጠውና የዋጠው በሚመስለው ወደ ጨለማው ውስጥ ተንሸራተተ።

ከዚያ እንዲህ ዓይነት መጪ ሁኔታን በመፍራት ባለ አስፈሪነት በተሞላ ሊያልፉት በማይችሉት ጨለማ ውስጥ በድጋሜ ብቻዬን ነበርሁ። ተስፋ-በማጣት እንደጠፋሁ ተሰማኝ። ይህ ራእይ አልነበረም፤ እውነታ ነበር። ኦህ በልቤ ውስጥ የነበረው ጥልቅ ኀዘን፣ ጥልቅ ጭንቀት፣ ቅዝቃዜ። መፅናናት አልነበረም፤ የአንድ የጠፋ ነፍስ አስጨናቂ ድንገተኛ ህመም ብቻ ነበር።

በመንፈሴ፥ “ኢየሱስ ሆይ፥ አድነኝ!” ብዬ ጮኽኩኝ። ወደ ላይ ስመለከት ዓይኖቼ የመሬትን የውጫዊ ክፍል ዙሪያና በዚያም ኢየሱስ ቆሞ ማየት ችለው ነበር። እርሱ ማይሎች(ብዙ ኪሎሜትሮች) ሩቅ ይመስላል። በዚያ ቅጽበት፥በምድር ላይ ቆሞ እንዳለ፥እየረዘመ የመጣውን እጁን ወደፊት ዘረጋው። እርሱ (ጌታ አምላክ አዳኝ የነገሥታት ንጉሥ እውነተኛ የዘላለም ሕይወትና መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ) ያዘኝና ወደ ራሱ ሳበኝ።

በአፓርትመንቴ (በመኖሪያ ቤቴ) ዳግም ተመልሼ በመንፈስ፣ በነፍስ፣ በሥጋ በጣም እየተንቀጠቀጥሁ ራሴን አገኘሁት፥ ነገር ግን በታላቁ አመሰገንሁት፥ ኦህ ለእኔ ሞቶ የነበረውን የግል አዳኜ የሆነውን የዓለሙን መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን እጅግ አመሰገንሁት (በዓለም መድኃኒት በኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ደስተኛ ነኝ)።

ለዚህ ልምምድ ምክንያቱ ምናልባት ሁለት-ጥምረት ይሆናል። በመጀመሪያ፥ ማብራሪያዎቻችንን አስመልክቶ ልንጠነቀቅ ይገባል። በዓይናችን በምናየው ወይም በጆሮአችን በምንሰማው በሰዎች ላይ መፍረድ የለብንም። በሌላ ቃላት፥እንደ ታሪካውያን ወይም ሌሎች እንደሚገልጿቸው ሰዎችን ልንፈርድ አይደለም። እግዚአብሔር እንደሚያደርገው ሰዎችን ለማወቅ ልንፈልግ ይገባል።

ከዚያ በተጨማሪ እጅግ አስፈሪው የሲኦል እውነታ በጣም ግልፅ ተደረገልኝ እና ነፍሳትን(ሰዎችን) ለማዳን በውስጤ መሻትን አስገኘ። ታላላቆች፣ እንዲሁም ትንንሾች፥ በአንድነት በሲኦል ታላቅ-መከራ(ችግር)ና ሥቃይ ውስጥ ተሸፍነዋል(ተውጠዋል)። በነገራችን ላይ፥በሥራ ባልደረቦቻቸው አድናቆት ይሰጣቸው የነበሩ ታላላቅ ሰዎች ለዘላለም በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሆነው ሌሎች ራእዮችን አይቻለሁ። በምድር ላይ ሳሉ ታላቅ መሆን አንድን ሰው ለመንግሥተ ሰማይ ተመራጭ(ብቁ፥qualify) አያደርገውም። ኢየሱስን በመቀበል ዳግም መወለድና በትክክል በቃሉ እየኖሩ በቀጥታ መራመድ ብቻ ወደ መንግሥተ ሰማይ ያስገባል።

እነዚህ ማብራሪያዎች ሰዎችን ወደ ሲኦል ከመሄድ ለማዳን በልባችን ውስጥ የሚቀጣጠል መሻት ያኑሩ።

# በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን ሃሌ ሉያ።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ እና ቶማስ ጌታቸው
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com,

Thomas Getachew, hithomasgetachew@gmail.com